ዴሞክራሲያ

ዴሞክራሲያ ቅጽ 35 ቁጥር 7 ሰኔ 2002 ዓ.ም

<u>ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል!</u>

ላለፉት 19 ዓመታት በወያኔ ደይን ውስጥ ፍዳ መጋትና መከራና ስቃይን መሸከም የተገደደው ሕዝብ ነገ ብሩህ ቀን ይመጣል በሚል ተስፋ ሲታገልና የደም ዋጋም ሲከፍል መቆየቱ የሚታወቅ ነው። ወያኔ ዓመታት ሲያልፉ የተወለደባትን ግን እንደ ባዕድ ጠላት የሚያያትን ሀገር ያዝንላት ያስብላት ይሆናል ብለው ቀጭን ተስፋን ያስተናገዱትም ቢሆኑ በወያኔ ዕብሪትና የግፍ ሥራ መሸማቀቃቸውና ስህተታቸውንም መገንዘብ የግድ ሆኖባቸዋል። ወያኔ አያሌ ጭምብሎችን ያጠለቀ ቢሆንም ሁሉንም አውልቆ፤ ማሞኘትና መደለል፤ ማባበልና ማንቆሻበል በቃኝ ብሎ ከነጭራቅ ፊቱ ብቸኛ ገዢ ፓርቲነቱን ይፋ አድርጓል።

የወያኔ አገዛዝ አጉል ተስፋን በምኞት ደረጃ እየመገበ፤ ለውጥ ሊመጣ ነው ከበሮን እየደለቀ ከዓመት ዓመት ብዙ ዜጎችን ማደናገሩ የሚካድ አይደለም። ገና ከደደቢት ሲነሳ ኢትዮጵያን መገነጣጠልና ትግራይን ነፃ ሬፑብሊክ ማድርግ ዕቅዴና ህልሜ ነው ብሎ ይፋ የወጣ ቢሆንም ይህንኑ በየማጠፊያው እያጠፈና ቀየርኩ እያለ አደናጋሪ ሰበካውን ሲጠርቅ ጆሮ የሰጡት ብዙዎች ናቸው። ኢሕአዴግ የተባለውንም ጭምብል ሲያጠልቅ እውነትም ኢትዮጵያዊ የሆነ መስሏቸው አጆሀ ያሉት ጥቂቶች አልነበሩም። ከታዘለ ከቶምና መቸም የማይወርድ አረመኔ መሆኑ ቢነገርም የአድማጭ ጆሮ ተዘግቶ ነበር ማለት ይቻላል። ልጅ ጨራሾቹን ወያኔዎች ልጆቼ ብለው ያቀፉና የደገፉትም የሚረሱ አይደሉም። ስንት ደም የፈሰሰለትን ሰንደቅ ዓላማ ብጣቂ ጨርቅ ብለውና የጫማቻው ማዘቢያ አድርገው እንዳልነበር ሁሉ፤ አማርኛ የተናገረን በከሀዲነት ሲከሱ እንዳልነበር ሁሉ ግልብጥ ብለው ከኛም በላይ ኢትዮጵያዊ ላፈር ሲሉ እሰየው ያሏቸውም ነበሩ። ከዘላቂ ወዳጅና ደሜ ካለውም ሻዕቢያ ጋር ጦርነት ሲገባ ወያኔ ወደብ ያስመልሳል ብለው ያመኑና በጦርነቱም ገብተው የተማገዱ--በርካቶችም ምንም ሳያስቡበትና ሳያሰላስሉ በዚያው ያለቁ-- ከመቶ ሺ በላይ መሆናቸውም የታወቀ ምፀታችን ነው። ወያኔ ብልጥ ሆኖ ነው ወይስ ዜጎች በተደጋጋሚ ተሞኝተው ነው የሚለው ጥያቄ መቅረቡ ደግሞ አግባብነት ያለው መሆኑ የሚካድ አይደለም። ሕዝብ ስህተቱን ከደጋገመ ለሚከተለው ጉዳትና ጥፋት በቅድሚያ ተጠያቂ ራሱ ብቻ ነው። የኢትዮጵያ

ሕዝብ በአብዛኛው የወያኔን አገዛዝ ፀረ-ዴሞክራሲነት ተረድቶ በ1997ሉ ምርጫ ሽንፈትን አከናንቦታል። ወያኔም ንፁህንን ፈጅቶ በጉልበቱ በሕገ ወጥ ሥልጣን መቀጠሉ የማይደበቅ ሐቅ ነው። ዋናው ቁም ነገር ግን ሕዝብ በሕዝብ ደረጃ ይህን አረመኔ አገዛዝ አንቅሮ መትፋቱና ወግድልኝ ማለቱ ነው።

አለመታደል ሆነና ሥር ነቀል ለውጥ ፈላጊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በየታሪካዊ ወቅቱ ድሉን እየተቀማ፣ መብቱ እየተገፋና መብቱ እየተረገጠ፣ ያልፈለገው እየመጣበት፣ ጨቋኝ እየሰፈረበት ሲቀጥል መቀበልን ተገዷል። በየካቲት 66ና በግንቦት 1983 የደረሰው ይህ ነው። ጨቋኝ በባሰ ወይም ባልተናነሰ አምባገነን ተተክቷል። የአሁኑ ደግሞ ከሥልጣን ባሻገር ሀገርንም በጥላቻ አይቶ ሊሰነጣጥቅ፣ ሊያዋርድና ሊያጠፋ የተነሳ በመሆኑ ልዩ አውሬ ሆኖ ተደቅኖብናል። ኢትዮጵያን የሚያቀልና የሚያደባይ ማንኛውም ክስተት ቀልቡን ይስበዋል። ሀገሪቷን ለባዕዳን በዝባዦች ከፍቶ መስጠቱ ሳይበቃ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ የሀገሪቷን መሬትም ቆርሶ ለባዕድ ሀገር ለግሷል። ለመጀመሪያ በሀገራችን ታሪክ በአባይ ላይ ዓይናቸውን የጣሉትን ግብፆች በጣና ሐይቅ- ባሕር ዳር አካባቢ መሬት ሰጥቷል። ብዙ ሺዎችን አፍኖ ያሰቃያል፣ ለሕዝብ የታገሉትን እነ ፀጋዬና ስንቶቹንም ደብዛቸውን አጥፍቷል። ይህ ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን በሥልጣን ለጥቂት ዓመታትም መቆየት የነበረበት አለመሆኑ ግልፅ ሆኖ ሳለ፣ በመጀመሪያው ሰሞን የነበረው መደናገርና እንያቸው ዘይቤ እንደ ጤዛ ተኖ ጠፍቶ እየታየ ወያኔ ግን 19 ዓመት በሥልጣን መቆየቱ ከአፈናው ባሻገር በሕዝብ ጎራና ድርጅቶቹ ዘንድ አሳሳቢ ድክመት መኖሩንም ጠቋሚ ነው ማለት አለብን። በዓይንህ ያለውን ጉድፍ መጀመሪያ አፅዳ እንደተባለው ሀገርን የማዳኑ ተግባር የሌሎች ሳይሆን የራሱ የሕዝብ በመሆኑ ድክመትን በተመለከተ ለቀቅተኛ ሳይሆን ማስወገድ ማረም ይገባዋል ማለት ነው--ተጠናክሮ ጠላትን ለማጥቃትና ድልን ለመቀዳጀት። ያለፈው አልፎ ቢያንስ ከ 1997ሉ ክስተትና ከተከተለውም ሰቆቃ ስለ ወያኔ የሞላ የተትረፈረፈ መረጃን ያገኘን ሲሆን ይህንንም ማጤን ከብዶ ዳግም ስህተትን በ2002 መድገም የተገደዱ ኃይሎች መኖራቸውን ሕዝብ ታዝቧል። ዳግም ወያኔ ሲያላግጥና ምርጫ ቧልቱን በራሱ ፍፁም አሸናፊነት ሲደመድም ማየትም የተገደዱት ተስፈኛ ተፎካካሪዎችም ከዚህ ሁሉ በኋላ አሁንም በዚያው በከሰረው የፖለቲካ መስመርና ስልታቸው ለመቀጠልና በዚሁም ሕዝብን ጎትተው መቀለጃ ለማድረግ ከወሰኑ ለአንዴም ለሁሌም ከሕዝብ መነጠላቸውና ራሳቸውን ለከፋና ለባሰ ውድቀት መዳረጋቸው አይቀሬ ይሆናል።

ገልጠን እንየው ስንል ደግሞ ድርጅቶች የሕዝብ ትግል መሪ ነን ወይም አራማጅ መሣሪያ ነን ለማለት የሚችሉት እውነትም ሕዝብን ሊመሩ፣ ሁኔታዎችን በሚገባ በጊዜ መርምረው ተገቢውን ስልት ሊቀይሱ ሲችሉ፣ ቆራጥና ፅኑዕ ሆነው ሲገኙና መልዕክታቸውንም ለሕዝብ ማድረስ ሲችሉ ነው። ለሕዝብ ጭራ ከሆኑ ወይም ወደፊት ተስፈንጥረው ከሕዝብ ከራቁ ትግልን ሊመሩ አይችሉም--ፅንፈኛ ፖለቲካ በየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን ብስለትን ሳይሆን

ስህተትን የሚያሳይ ነውና:: ባለፉት ዓመታት ወያኔ የፖለቲካ ድርጅቶችን ሊያደናግርና ሊያጠቃ፣ ሊከፋፍልና በአንጻ አንበጣ ሊያስወርር ሞክሮ ተሳክቶለታል ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ድርጅቶች በተባበረ መንገድ መታገል እያቃታቸውና አልፎም እርስ በርስ እየተጠላለፉና ለወያኔ ሰርጎ ገብ በጥባጮች ሰለባ እየሆኑ ትግሉ ሲጎዳ ቆይቷል:: ወያኔ ለአገዛዝ ተቃዋሚ ነን ያሉትንም በስልት እየቃኘ፣ ያልሆነ አቅጣጫና ትኩረትንም እየሰጠ መቆየቱንም ማመን ያስፈልጋል:: ከጉንዳን ደም ፍለጋ እንዲሉ ከወያኔ አገዛዝ የዴሞክራሲ ጭላንጭል ይታያል ወይም የዴሞክራሲ በር ገርበብ፥ ከፈት ይላል በሚል ቅዠት - ሕዝብ በዋና ደረጃ የሰለቸው ለመብቱ መዋጋት ሳይሆን በጭቆና መቀጥቀጥ ሆኖ ሳለ - ሕዝብ ጦርነት ሰልችቶታል፣ በ "ሰላም እንታገል" የሚል አጓጉል ሰበካ ሰፍኖ፥ ብረት ያነሱትንም በይፋ ማውገዝ ብልህነትና ባለመላ መሆን ነው ተብሎ፣ መደረግ የነበረበረትና ያለበት ትግል ሲጓተትና ሲደናቀፍ መቆየቱም መታወቅ አለበት:: ሆኖም ሀገርን የማዳኑ ተግባር ዛሬም ሰልፍንና ተግባራዊ ትግልን ጠያቂ ነውና ዘግይቶም ቢሆን "ተነስ ለሀገርህ!" የሚል ነጋሪት መጎሰሙ ወቅታዊና ተገቢም ነው::

"ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው" ሲበደል እንደተባለው የወያኔ 19 ዓመት ሥልጣን ሕዝብና ሀገርን አስለቅሷል፣ በደሉ ሞልቶ ፈሷል፣ ሕዝብና ሀገርንም ሊያጠፋ ቃጥቶታል:: ወያኔም በማያወላዳ መንገድ ማንነቴን ዘረኝነቴን አልቀይርም፣ መጀመሪያም እኔን ማመናችሁ ስህተት የአሁኑ ደግሞ የእብደት እብደት ነው እያለ ነው:: የወያኔ አገዛዝ ያለፈውን 19 ዓመት ባስከፊ መንገድ ሊደግም፥ ሊያባብስ ተዘጋጅቶ ያለ ሲሆን ሕዝብንም በጦርነቶች ሊማግድ፣ በብሔረሰብና ሃይማኖት ግጭቶች ሊያፋጅ ተነስቷል:: ሕዝብ ወዳጅ ጠላቱን በሚገባ ለይቶ፣ እርም በሚያወጣበትም አውጥቶ የሚገኝ ሲሆን በሕዝብ ጎራ እየተሽሎኮለኩ የወያኔን እርኩስ ተልዕኮ ሊያሚሉ የሚጥሩትንም ከሀዲዎች ማንነት ጠንቅቆ ተረድቷል:: ትውልድም በጅምላ ታሪካዊ ግዳጁን የሚዘነጋ አይደለምና ብቁ መሪ ካገኘ አሁንም ደሙን ለሀገሩ ሊያፈስ ዝግጁ ሊሆን መቻሉን ሌላው ቢቀር በ1997ም መስዋዕት ሆኖ አስመስክሯል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ከውስጥም ከውጭም ህልውናውን አደጋ ላይ የሚጥሉ ኃይሎች አሰፍስፈው ባሉበት ሊዘናጋ አይጠበቅምና በሁሉም መንገድ--በተለይም በሁለገብ መንገድ--መታገሉ ብሔራዊ ግዳጁ ነው:: ይህን ቅዱስ ትግል ለማካሄድ ከማንም ቢሆን ፈቃድ እንዲጠይቅም መጠበቅ የለበትም:: ሀገሩን ለማዳንና መብቱን ለማስከበር ማካሄድ ያለበትን ትግል ዓይነት የሚወስነው ያለው ተጨባጭ ሁኔታ እንጂ ራሳቸውን የሰላም ጳጳስ ብለው የሰየሙ አወቅን ባዮችና ወያኔ ሊሆኑ አይችሉም:: ሁለገብ ትግል ፍቱንና ወቅታዊ መሆኑን ሲጠራጠሩ ለነበሩት ሁሉ ወያኔ ራሱ የምርጫና ሰላማዊ ትግል የምትሉት ሁሉ እነሆ አከተመ ብሎ በዕብሪት መልዕክቱን በግንቦት 2002 አስተላልፏል:: አሁንም ለማጭበርበር፣ ለመሸንገል፣ ለመከፋፈል ልዩ ልዩ አሳሳች ቅጥረኞቹ አማካይነት እየጣረ ያለ ቢሆንም ምንም ሆነ ምን የማይቀየረው መሰረታዊ ሐቅ ግን ወያኔን በሁለገብ ትግል ታግሎ ከማስወገድ ሌላ ምንም

መንገድ እንደሌለ ነው:: ሽክም የከበደውና የመረረው ሕዝብ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሸፈት፣ በማመፅ፣ ብረት አንስቶ ፋኖ በመሆንና የወያኔን ዕብሪት በማስተንፈስ ማረጋገጥ አለበት:: ይህን በተፃረረ የሚሰበክና የሚወሳ ሁሉ ለወያኔ አገዛዝ ዕድሜ ቀጣይና ሀገርን አጥፊ ነውና ሕዝብ ጆሮ ሊሰጠው አይጠበቅም::

ደም እንደጠማው ጨካኝ ሽብርተኛ የወያኔ ቡድን በኢትዮጵያ ላይ ብዙ ፈንጂዎችን አጥምዶ እንዳለም መዘንጋት አይገባም:: በብሔረሰብ ደረጃ ሕዝብን ከፋፍሎ ለማጫረስ የጀመረውን ቀጥሎበታል:: ይባስ ብሎ በሃይማኖት ደረጃም ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲጨራረስ ለአክራሪዎች በር ከፍቶ መሠረት እየጣለ ነው:: የሀገራችንን መሬት ለሱዳን አስረክቦ ሉዓላዊነታችንን አስደፍሯል:: በአባይ ጥያቄ ሲከተል የቆየው መንገድ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ያስቀደመ ካለመሆኑ ሌላ በአሁኑ ጊዜ ተገልብጦ ሊያሰማን የሚፈልገው ግብፅን ተፃረርኩ ጩኸት ደግሞ በሀገሪቷ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ከመቋቋም አንፃር ያደረገው ዝግጅት ሆነ ያካበተው የሕዝብ አመኔታና ድጋፍ ከቶም የለውም:: በሰሜን ተካሂዶ ለብዙ ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነውን ጦርነት እንደገና ሊጭር ወታደርና መሳሪያ ወደ ግንባር እያጓጓዘ መሆኑ ምስጢር አይደለም:: ባለፈው መንፈስ የሚዋጋለት ወታደርም ወይም ድጋፍ ሊሰጥ የሚነሳ የሕዝብ ክፍል አለመኖሩ ለወያኔ ካልታየው መቸም ታውሯል ማለት ነው:: የሻዕቢያ ተቃዋሚዎችንም በአዲስ አበባ በአስቸኳይ ተሰብሰቡ ግፊት ሊያገኝ የሚፈልገው ውጤት ጉም ነው:: በቅድሚያ አፋርና ኩናማዎችን ከዚያ ሳሆ/አሳወርታና ሌሎችን አናሳ ብሔረሰቦችን አሰባስቦ ለጥቆም የሻዕቢያ ተቃዋሚዎችን "ብሔራዊ ስብሰባ" ሊጠራ ቢያቅድም የራሱ ታዛዥ የሆኑትን ቡድኖች ሊያስቀድም መፈለጉ ዕቅዱን ሳያበላሸበት አይቀርም ብለው ታዛቢዎች የሚተቹት መሠረተ ቢስ ነው ሊባል አይቻልም:: ወያኔ እነዚህን ሰብስቦና ሸፋን አድርጎ ወደ አሥመራ መጭ ሊል አቅዷል የሚለው እንዳለ ሆኖ ይህ ቢሳካለትም ሌላ የባሰ ችግርን ያስከትላል እንጂ መፍትሄን ወይ ሰላምን የሚያመጣ ሊሆን አለመቻሉ ግልፅ ነው:: የትግራይ ትግሪኚ ህልምም በዚያው ደረጃ ያረፈ በመሆኑ በወረራ ህይወት የሚዘራ አይሆንም:: በኦጋዴን ጦርነቱ እየተባባሰ ነው:: ሌሎች ኃይሎችም በተቻለው ፍጥነት በትጥቅ ትግል ሊሰማሩ እያቀዱ መሆናቸውን ወያኔም የሚያውቀው ነው:: ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው የወያኔ አገዛዝ አንጂ ማንም ሌላ ኃይል አይደለም:: በሀገሪቷ ዴሞክራሲ በመጥፋቱና ወያኔ ጭፍን አምባገነንነትን በማስፈኑ ከማመፅ ሌላ መፍትሔ የለም--አለመኖሩንም ራሱ ወያኔም ባለፈው ምርጫ ባለው ቲያትሩ በሚገባ ግልፅ አድርጎታል::

ኢትዮጵያ ያለችበት አካባቢ በአጠቃላይ ወደ ከፋ ቀውስ እየተንደረደረ መሆኑ ደግሞ በሀገራችን የነገ ሁኔታ ላይ ያለው ጫና በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: ወያኔ በአንድ በኩል የሱዳን ወዳጅና አጋር ነኝ ቢልም በተለመደ መሰሪነቱ ደግሞ ደቡብ ሱዳንን ለማስገንጠል

ከምዕራባውያን ጋር እየሠራ ነው:: ለመጪዋ ነፃ ደቡብ ሱዳን የሚያገለግሉ የደቡብ ሱዳን መኮንኖች በመቀሌ አካበቢ በምስጢር ሥልጠና እየተሰጣቸው መሆኑን ሱዳንም አውቃለች:: የሱዳን አምባገነን ኦማር ኣል በሺር ግን ምንም እንኳን ለነሱ ታዛዥ የሆነ ሚሊሺያን በደቡብ ሱዳን ቢያዘጋጅም የግንጠላ ሴራውን ከመቋቋም አንፃር ዝግጅቱ ደካማ መሆኑ የሚታወቅ ነው:: በዚህም ተባለ በዚያ ግን በመጪው ዓመት በደቡብ ሱዳን የሚደረገው ውሳኔ-ሕዝብ ለመደረጉ አስተማማኝ ሁኔታ ካለመኖሩ ሌላ፣ ተደርጎ ግንጠላ ቢፀድቅም ጦርነትና ብጥብጥ አይቀርም ማለት ትክክል ነው:: የግንጠላውም ወረርሽኝ ወደ ዳርፉርም ተዛምቶ አካባቢውን ይበልጥ ማመሱና ማቃወሱ የሚጠበቅ ይሆናል:: ይህ ሁሉ ለሀገራችን ሕዝብ ትግል የሚኖረውን አንደምታ በጊዜ ማወቁ ደግሞ አስፈላጊ ነው:: ምንም እንኳን የኢትዮጵያን የነገ ሁኔታ ወሳኙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሆንም ሁኔታችን ላይ የባዕዱም÷ የቅርቡም የሩቁም ሁኔታ ጫና ያለው መሆኑን ልንዘነጋ አይገባም:: የወያኔ ቡድን ለም መሬት የለገሳቸው ባዕዳንም ጥቅማቸውን ጠባቂ የወያኔ አገዛዝ ነው ብለው ያምናሉና የሕዝብን ሉዓላዊነት አስከባሪ ትግል መፃረራቸው የማይቀርና መጠበቅም ያለበት ነው:: በመሆኑም ሀገረ ወዳድ ኃይሎች ይህን ሁሉ በሚገባ በሚዛን አስገብተው ተገቢውን አያያዝና ስልት ቀርፀው በሥራ ማዋል አለባቸው:: ሁለገብ ትግል ሁለገብ ምርምርና ቅኝትን ጠያቂ ነው--ዋና የማይችል ወሳጅ ወንዝ ውስጥ ዘው ብሎ ሊገባ አይጠበቅም::

ከመነቃቀፍ ይሻላል መተቃቀፍ ይላሉ አዋቂዎች:: በሌላ በኩል ደግሞ ካለፈው ካገደመው፣ ከባንዳውም ከነፍሰ ገዳዩም፣ ከሽብርተኛውና ቀይ ሽብርን ከሚክደውም፣ ከባዕድ ቅጥረኛውም ጋር መተቃቀፍ ብልህነት ሳይሆን ጅልነት መሆኑ ግልፅ ነው:: ሰነፍ ሲኮራ ማጭድ ይታጠቃል ተብሎ እንዳይቀለድብንም ማሰቡ አስፈላጊ ነው:: ላመረረ ትግል በተጨባጭ መነሳት፣ መደጋገፍ አለብን:: በአሁኑ ጊዜ የት ደርሰናል የሚለውን ስንመልስ ከላይ እንደተገለፀው ሀገር አጥፊው ወያኔ በግልፅም በዕብሪትም ፍፁም አምባገነንነቴን እዩልኝ ብሎ ተሰይሞ ሀገሪቷን ሊያደቅ መቀጠሉን እናያለን:: ዛሬ ወያኔ በምርጫና በሰላም ከሥልጣን ይወገዳል የሚለው የሞኝ ቀረርቶ ሊሰማ ፈቃድ ልንሰጥ አይገባም--"አለቀ ደቀቀ በቃ ተከተተ" ማለት ይገባል በታህሳስ 53 መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጊዜ ተብሎ እንደነበረው:: ያ ህልም ቅዠት ሆኖ ሕይወትንም ቀጥፎ በራሱ በወያኔ ተቀብሯል:: ዛሬ ወቅቱ ለሁለገብ ትግል፣ ለ'ፋኖ ተሰማራ በዱር በገደሉ ደግሞም በከተማ' ለሚል የታጋይ መዝሙር ማስተጋቢያ ነው:: ወቅቱ የሕዝብን የትግል ጎራ ከሚያደፈርሱ አስመሳዮችና የወያኔ ሰርጎ ገቦች የምናጠራበት ነው:: በትግልና በሕዝብ ስም የሚነግዱትን የምንለይበት ነው:: ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን የሚያጋጩና የሚከፋፍሉትን ትኳኖች የምናራግፍበት ነው:: በሕዝብ ጎራ ብዥታ ከተወገደና አስመሳዩ ከሐቀኛ ታጋዩ ከተለየ-ከተበራየ፣ በርና አጥር ለወያኔ ቅጥረኞችና ከፋፋይ አንጃዎች ዝግ ከሆነ ሀገር አድን ትግሉ በሚገባው መንገድ ሊካሄድ የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል::

ይህ በመሆኑም ኢሕአፓ ላለው ተጨባጭ ሁኔታና ትግሉ ለሚጠይቀው ምላሽ ለመስጠት ለሀገር ወዳድ ኃይሎች ሁሉ ያቀረበው ጥሪ ወቅታዊ ሆኖ ይገኛል። ምን ማድረግ አለብን ለሚለው አንገብጋቢና ከባድም ጥያቄ የመልስ መጀመሪያው በኢትዮጵያ አንድነት ሥር አንድ ኢትዮጵያውያን ምላሽ ለመስጠት እንስማማ የሚል ነው። በወንደሜና እህቴ ግንባር ደም አልይ ለማለት ወንድም እህት መሆናችንን መቀበል አለብን--ኢትዮጵያዊነታችንን ለድርድር ልናቀርብ የሚጠበቅም አይደለም። ችግሮቻችንን በሞላ በኢትዮጵያ ጥላ ሥር በዴሞክራሲና በመዋዋጥ ልንፈታ እንችላላን ብሎ ማመን መቀበል የመጀመሪያው ለድርድር የማይቀርብ ቅድመ ሁኔታ ነው። ተጨባጭ ሁኔታ እየሰጠ ያለውን ትምህርት በሚገባ ተረድቶ ወደ ድል ለመጓዝ ሁኔታው የሚጠየቀው የትግል ስልት ሁለገብ ትግል በመሆኑ ከወያኔ አገዛዝ ጋር በዚህ በዚያም መልክ ሊተሻሹና ሊተቃቀፉ የሚፈልጉት ሁሉ የቀጣዩ ጉዞ ተጓዳኝ ሊሆኑ የሚችሉበት መንገድ የለም። ለዚህም ነው በሁለገብ ትግል የሚያምኑት ሁሉ እና ብቻ ይወያዩ፣ ይነጋገሩ፣ ዕቅድና ትልም በጋራ ለማውጣት ይምከሩ የሚለው ጥሪ የቀረበው። ድርጅት ሲሉ ድርጅት ስንል በሚል መንፈስ አታካራ ውስጥ መግባት ባይጠቅምም--ለአፍ ዳገት የለውምና ሁሉም ባሻው የፈለገውን ነኝ ማለት በመቻሉ--ድርጅት ሊባሉ የሚችሉት ምን ምን መለኪያን ማሟላት አለባቸው የሚለው መልስ ማግኘቱ አስፈላጊ ነው። ኢሕአፓ በዚህ በኩል ብዙም ንትርክ ሳይገባ ሶስት አራት አባል ካላቸው ሳይቀር በህብረት ተጣምሮና እኩል ድምፅ ይዞ ሊታገል መሞከሩ የሚታወቅ ቢሆንም ይህ ሂደት ከጥቅሙ ጉዳቱ መብዛቱ ዛሬ የሚገመገም ሐቅ ነው። ነውናም የፖለቲካ ድርጅት ስንል በተጨባጭ ለትግሉ አስተዋፅዖ ያደረጉና ሊያደርጉ የሚችሉ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት። በእንቅስቃሴ የተሰማሩ፣ አባላት ያሏቸው፣ ለሁለገብ ትግሉ በሰውም በሌላም የበኩላቸውን የሚታይ አስተዋፅዖ ሊያደርጉ የሚችሉ መሆን አለባቸው። በአሁኑ ወቅት ከሀገራችን ትግል አንፃር ድርጅት ስንልና ውይይትና ትብብር ሲጠራ በቅድሚያ የሚመለከተውም መሰል ድርጅቶችን ነው። የከዚህ በፊት የህብረትና ቅንጅት ተመክሮዎችን ሁሉ ስንመረምር--የሰጡት ጠቀሜታ እንዳለ ሆኖ-- አሞራና ቅል ተጋቡ፣ አሞራው በረረ ቅሉም ተሰበረ ዓይነት መሆናቸውን መካድ አንችልም።

ወያኔ የተባለውን ጋኔን ከማስወገዱ በተጨማሪ ወያኔም የፈጠራቸውን ወይም ያባባሳቸውን የኢትዮጵያን ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት የምልዓተ ሕዝቡ ተሳትፎና ጥረት ወሳኝና አስፈላጊ ነው። የግለሰቦችና የአንድ ድርጅት ቀመር መፍትሔ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ አይታይም-- መመካከር፣ በጋራ መጣር፣ መዋዋጥና መቻቻል ከሁሉም በላይ የሕዝብን ቀጥተኛና ነፃ ተሳትፎ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። እናውቅልሃለን ማለቱና በሕዝብ ላይ በምርጥነት መጀነኑን ትቶ ከሕዝብ ለመማርና የልቡን ትርታ ለማዳመጥ ዝግጁና ትሁት ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል። በድሮ በሬ ለማረስ መነሳቱ አያዋጣምና ቅኝትም አመለካከትም ተህድሶን ይዞ መነሳት አለበት። ግን ዘመናዊና አዲስ ነን ለማለት ወይም የሰለጠነ ፖለቲካ

መስመርን ይዘናል በሚል ሽፋን ለጠላት መጎንበስን፣ ለባዕድ መስገድንም መቃወም ይኖርብናል ማለት ነው። ዓመታት ተቆጥረዋል፣ በወያኔ ጫማ ሥር ሀገራችን ወድቃ መከራ ታያለች፣ የሕዝቧ እንባና ደም መፍሰስ አላቆመም። ስለ መከራችን መጮሁ አብቅቶ መከራ ያመጣብንን ለማስጮህ መነሳት እንዳለብን ወያኔ ራሱ ሳይቀር እየነገረን ነው። የቆረጠና ያመረረ ሁለገብ ትግል በወያኔ ላይ መካሄድ አለበት። ለዚህ ትግል ስምሪት ሆነ ስኬት ኢሕአፓ በራሱም ተጠናክሮ ለመገኘት ሆነ ከሌሎችም ለመምከርና የትብብርን መፍትሄ ለመሻት ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ዝግጁ ነው።

ሀገርን ለማዳን መሸፈት፣ ማመፅ፣ አሻፈረኝ ብሎ ዱር ቤቴ ማለት ሲያንሰን ነው!
ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል ነውናም ለቁርጥ ቀን ትግል በጋራ እንነሳ!!
እናቸንፋለን!!!